**የኢንዱስትሪ ኬሚካል የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት አሰጣጥ፣ የምዝገባ እና አግባብ ያላቸው አካላት የሚያስተዳድሯቸው ኬሚካሎች የመረጃ አያያዝ ረቂቅ መመሪያ ቁጥር - - - /2017ዓ/ም**

የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር፤ የአስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር መወሰኛ አዋጅ ቁጥር 1263/2014 አንቀጽ 19 ንዑስ አንቀጽ 4 ፣ የኢንዱስትሪ ኬሚካሎች ምዝገባና አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 1075 አንቀጽ 6 እና 8 መሠረት ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

1) **አጭር ርዕስ**

ይህ መመሪያ "የኢንዱስትሪ ኬሚካል የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት አሰጣጥ፣ የምዝገባ እና አግባብ ያላቸው አካላት የሚያስተዳድሯቸው ኬሚካሎች የመረጃ አያያዝ መመሪያ ቁጥር - - - /2017ዓ/ም" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2) **ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ ፤

1. " የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት" ማለት በአዋጁ አንቀጽ 5 መሠረት በሮተርዳም ስምምነት እና የአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን በሚያወጣው መመሪያ ጥብቅ የአጠቃቀም ገደብ ከተጣለባቸው የኢንዱስትሪ ኬሚካሎች ውጪ የሆኑ የኢንዱስትሪ ኬሚካሎችን ለማምረት፣ ወደ ሀገር ውስጥ ለማስገባትና ለመጠቀም የሚያስፈልጉ መስፈርቶችን ያሟላ መሆኑን በማረጋገጥ በሚኒስቴሩ የሚሰጥ የምስክር ወረቀት ነው፣
2. "የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ሰጪ" ማለት የኢንዱስትሪ ኬሚካልን ለማምረት ወይም ወደ ሀገር ውስጥ ለማስገባት የሚያስችል የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የሚሰጥ ፣ በሀገር ውስጥ የተመረቱ እና ከውጭ ሀገር ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ የኢንዱስትሪ ኬሚካሎችን ምዝገባ የሚያከናውን እና ብሔራዊ የኬሚካል መዝገብ አደራጅቶ የሚይዝ በሚኒስቴሩ ስር የሚገኝ የሥራ ክፍል ነው፣
3. " የኬሚካል ትንተና የምስክር ወረቀት (Certificate of Chemical Analysis (COA) " ማለት በኬሚካል ላይ የተደረገ ሳይንሳዊ ምርመራ ውጤትን ፣ ኬሚካል ማምረት ሂደት ጥቅም ላይ የዋሉ ግብዓቶችን፣ ኬሚካሉ የተመረተበት እና የአገልግሎት ማብቂያ ቀንን የሚያመለክት ሰነድ ነው፡፡

1st DRAFT

4. “ የቁስ ደህንነት መረጃ ወረቀት (Material safety data sheet (MSDS) ”ማለት ለምርቱ መጋለጥ የሚያስከትለው የጤና ጠንቅን፣ ከምርቱ አያያዝ፣ ማከማቻ እና አጠቃቀም ጋር የተገናኘ የአደጋ ግምገማን፣የአምራች ሠራተኞች ለምርቱ የመጋለጥ አደጋን የመከላከያ እርምጃን፣የአደጋ ጊዜ ሂደቶችን እና ደኅንነቱ የተጠበቀ የአጠቃቀም መመሪያዎችን ያካተተ ሰነድ ነው፡፡

5. “ የምርት መለያ ቁጥር (Product Batch Number) ” ማለት አንድ የምርት አብረው ከተመረቱ ምርቶች መካከል ለመለየት የሚያስችል መለያ ኮድ ሲሆን ምርቱ ከተመረተበት አንስቶ እስከ ስርጭት እንደዚሁም ከሽያጭ በኋላ ለመከታተል እና ለማስተዳደር የሚረዳ ነው፡፡

6. “ የተጣጣመ የሸቀጦች አሰያየምና አመዳደብ ሥርዓት (Harmonized System code(HS code))” ማለት በአለም አቀፉ የጉምሩክ ትብብር ምክር ቤት ስምምነት(ኮቬንሽን) የፀደቀ የሸቀጦች አመዳደብ ሥርዓት ሲሆን በአለም አቀፍ ንግድ ውስጥ የሚዘዋወሩ ሸቀጦች ወጥ በሆነ መልኩ የየራሳቸው መለያ ቁጥር ወይም ኮድ እንዲኖራቸው የሚደረግበት ሥርዓት ነው፡፡

7. “የስሪት ሀገር ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት (Certificate of Origin) ” ማለት አንድ ምርት የተመረተበትን ሀገርን የሚያረጋግጥ የሰነድ ማስረጃ ነው፡፡

8. “ የጎጂነት ባህሪ ምደባ (Hazard classification) ” ማለት አንድ ኬሚካል አደገኛ መሆኑን ለማወቅ እና የአደገኛነቱን ተፅእኖ የክብደት ደረጃ ለመለየት መረጃዎችን የመገምገም ሂደት ነው፡፡

9. “ አግባብ ያላቸው አካላት የሚያስተዳድሯቸው ኬሚካሎች ” ማለት በኢትዮጵያ ግብርና ባለሥልጣን ምዝገባና ቁጥጥር የሚካሄድበት ፀረ ተባይ፣ በኢትዮጵያ የምግብ እና የመድሐኒት ባለሥልጣን አደረጃጀት ምዝገባና ቁጥጥር የሚካሄድበት - - - እና ሌሎች አካላት የሚመዘግቧቸው እና ቁጥጥር የሚያደርጉባቸው ኬሚካሎችን ያጠቃልላል፡፡

10. “ጂኦግራፊካል ኢንፎርሜሽን ሲስተም (ጂአይኤስ)” ማለት በኮምፒውተር በመታገዝ የጂኦግራፊያዊ መረጃን ለመያዝ ፣ ለማከማቸት ፣ ለመተንተን እና ለማስተዳደር የተዘረጋ ስርዓት ሲሆን በቦታ ላይ ተመስርቶ የኢንዱስትሪ ኬሚካል የማከማቻ መጋዘን፣ የማምረቻ ቦታን እና ሌላ የመገኛ ካርታን የሚያመለክት ነው፡፡

11. “ድብልቅ የኢንዱስትሪ ኬሚካሉ” ማለት - - - -

1st DRAFT

12. "ዲጅታል ኢንኮድንግ ሲስተም" ማለት - - - -

13. "አስመጪ " ማለት ለንግድ ወይም ለንግድ ላልሆነ ዓላማ የኢንዱስትሪ ኬሚካልን በሕጋዊ መንገድ ወደ ሀገር ውስጥ የሚያስገባ ሰው ነው፡፡

14. "አዋጅ" ማለት የኢንዱስትሪ ኬሚካሎች ምዝገባና አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 1075/2010 ነው፣

15. "ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር" ማለት እንደቅደም ተከተሉ የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ወይም የኢንዱስትሪ ሚኒስትር ነው፣

16. "ሰው" ማለት ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፡፡

17. ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለጸው አነጋገር ሴትንም ይጨምራል፡፡

18. በአዋጁ አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 9 እና 13 በስተቀር በአዋጁ አንቀጽ 2 ላይ የተሰጡ ትርጓሜዎች ለዚህ መመሪያም ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

3) <u>የተፈጻሚነት ወሰን</u>

ይህ መመሪያ በሀገር ውስጥ በሚመረቱና ከውጭ ሀገር ወደ ሀገር ውስጥ በሚገቡ የኢንዱስትሪ ኬሚካሎች እና አግባብነት ያላቸው አካላት በሚያስተዳድሯቸው ኬሚካሎች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

4) <u>ዓላማ</u>

ይህ መመሪያ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፤

1. የኢንዱስትሪ ኬሚካሎችን ለመመዝገብ እና ለማስተዳደር የሚያስችል ሀገራዊ ሥርዓት ለመዘርጋት፣
2. ከኢንዱስትሪ ኬሚካሎች እንቅስቃሴ ጋር በተያያዘ በሰው እና በእንስሳት ጤና እንዲሁም በአካባቢ ደህንነት ላይ ሊከሰቱ የሚችሉ ጉዳቶችን ለመከላከል እና ለመቆጣጠር፣ እና
3. አግባብ ያላቸው አካላት የሚያስተዳድሯቸውን ኬሚካሎችን መረጃ ለመያዝ የሚያስችል ሀገራዊ ሥርዓት ለመዘርጋት፡፡

1st DRAFT

## ክፍል ሁለት

## የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ሰጪ አካል ስለመሰየም እና ስለብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት አሰጣጥ

5) **የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ሰጪ አካል ስለመሰየም**
   1. በሚኒስቴሩ የብቃት ፈቃድ እና አገልግሎት መሪ ሥራ አስፈጻሚ የኬሚካል ፈቃድና ምዝገባ ዴስክ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ሰጪ እንዲሆን በዚህ መመሪያ ተሰይሟል፡፡
   2. የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ሰጪው ኃላፊ በሥራ ክፍሉ የሚሰጠው የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት በዚህ መመሪያ መሠረት ስለመሰጠቱ የማረጋገጥ ኃላፊነት አለበት፡፡

6) **የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ሰጪው ተግባርና ኃላፊነት**
   1. አመልካቾች የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለማግኘት ጥያቄ ሲያቀርቡ በዚህ መመሪያ የተዘረዘሩ መስፈርቶች መሟላታቸውን በማረጋገጥ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፣ ያድሳል፣ ያግዳል፣ይሰርዛል፡፡
   2. በዚህ መመሪያ ክፍል ሦስት መሠረት የኢንዱስትሪ ኬሚካሎችን ይመዘግባል፡፡
   3. በዚህ መመሪያ ክፍል አምስት መሠረት የኢንዱስትሪ ኬሚካሎችን እና አግባብ ያላቸው አካላት የሚያስተዳድሯቸውን ኬሚካሎች ሀገራዊ የመረጃ አደራጅቶ ይይዛል፡፡
   4. በዚህ መመሪያ አፈፃፀም ሂደት ስላጋጠሙ ተግዳሮቶች ፣ ስለመስፈርቶች ክለሳ እና ሌሎች መመሪያውን ለማሻሻል የሚረዱ ሐሳቦችን በማዳበር የውሳኔ ሐሳቡን ለበላይ ኃላፊዎች ያቀርባል፡፡
   5. ለዚህ መመሪያ አፈጻጸም የሚረዱ መረጃዎችን ሁሉ አደራጅቶ ይይዛል፡፡
   6. ለዚህ መመሪያ አፈጻጸም የሚረዱ ቅጾችን ያዘጋጃል ወይም የተዘጋጁትን አሻሽሎ ያዘጋጃል፡፡
   7. የተሰጡ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀቶች ብዛትና የተሰማሩበት የዘርፍ ዓይነት መረጃዎችን በመተንተን የማሰራጫ ዘዴዎችን በመጠቀም ተደራሽ ያደርጋል፡፡
   8. ወቅታዊ መረጃዎችን በማደራጀት ለበላይ ኃላፊዎችና ለሚመለከታቸው አካላት ሪፖርት ያቀርባል፡፡

7) **የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የመያዝ ግዴታ**

1st DRAFT

1. ማንኛውም ሰው የኢንዱስትሪ ኬሚካልን ለማምረት ወይም ወደ ሀገር ውስጥ ለማስገባት ለሚኒስቴሩ በማስመዝገብ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት መያዝ አለበት፡፡
2. ከአምራች ወይም ከአስመጪ በመግዛት ወይም በስጦታ ወይም በማናቸውም ሌላ መንገድ የኢንዱስትሪ ኬሚካል የተላለፈለት ሰው አምራቹ ወይም አስመጪው የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ያለው መሆኑን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ማቅረብ አለበት፡፡

8) <u>**የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት መስፈርት**</u>

ማንኛውም ሰው የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለማግኘት የሚከተሉትን መስፈርቶች አሟልቶ ማቅረብ አለበት፤

1. ለዚሁ ዓላማ የተዘጋጀውን ቅጽ በመሙላትና በዚህ መመሪያ መሠረት የሚጠየቁትን ሰነዶች በማያያዝ ማቅረብ፣
2. የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ጠያቂው አምራች ወይም አስመጪ ነጋዴ ከሆነ በንግድ ሥራ ላይ የሚገኝ መሆኑን የሚያሳይ የንግድ ሥራ ፈቃድ ወይም የኢንቨስትመንት ፈቃድ፣
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ላይ የተጠቀሰው ተፈጻሚ የማይሆነው፤

   ሀ) የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ጠያቂው አስመጪ የኢንዱስትሪ ኬሚካሉን ወደ ሀገር ውስጥ ያስገባው ንግድ ነክ ላልሆነ ዓላማ ከሆነ እና ከሚመለከተው አካል የተሰጠ ወቅታዊ ደጋፊ ማስረጃ ማቅረብ ሲችል፣

   ለ) የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ጠያቂው ወደ ንግድ ሥራ ለመግባት በሂደት ላይ ያለ አምራች ወይም አስመጪ ከሆነ እና ይህንኑ ሂደት መጀመሩን የሚያመለክት ከሚመለከተው አካል የተሰጠ ወቅታዊ ደጋፊ ማስረጃ ማቅረብ ሲችል ነው፣

4. ለኢንዱስትሪ ኬሚካል ማከማቻና ማስቀመጫ የሚሆን መጋዘን በባለቤትነት ወይም በኪራይ ይዞታ ያለው መሆኑን ማረጋገጫ፣
5. የኢንዱስትሪ ኬሚካል የማከማቻ መጋዘን ካርታና ጂኦግራፊካል ኢንፎርሜሽን ሲስተም፣

1st DRAFT

6. የኢንዱስትሪ ኬሚካል ማከማቻና ማስቀመጫ መጋዘን ጂ.ፒ.ኤስ ኤክስ ዋይ ኮርድኔሽን፣ (Warehouse GPS X Y Coordination)
7. በኢንዱስትሪ ኬሚካል አያያዝ አግባብነት ያለው ትምህርትና ሙያ የተማረና የሰለጠነ ባለሙያ መቅጠሩን የሚያረጋግጥ ሰነድ (A document confirming the employment of an appropriate professional trained in the field (chemical management system))
8. **ደረጃውን የጠበቀ** የአስተዳዳር ቢሮ/standard administration offices with full office equipment's/
9. **ደረጃውን የጠበቀ** የእሳት አደጋ መከላከያና መቆጣጠሪያ ስርዓት /Standard Fire Protection and Control System/ እና
10. የድንገተኛ አደጋ መከላከያ እና መቆጣጠሪያ ስርዓት /standard Emergency prevention and control system/

ያለው መሆን ማረጋገጫ ማቅረብ አለበት።

## 9) <u>የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይዘት</u>

የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀቱ፤

ሀ) የግለሰቡ ወይም የድርጅቱ ሙሉ ሥም፣ አድራሻ

ለ) የኢንዱስትሪ ኬሚካል አምራች ወይም አስመጪ ወይም ለሚያመርተው ምርት በግብዓትነት ተጠቃሚ መሆኑን

ሐ) የየብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀቱ የተሰጠበት ቀን፣

መ) የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀቱ የአገልግሎት ዘመንና የዕድሳት ጊዜ፣

ሠ) የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ሰጪው ኃላፊ እና የሥራ ክፍሉ ኃላፊ ሥምና ፊርማ ፣

ረ) የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ባለቤት ፎቶግራፍ፣ እና

ሰ) የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ማኅተም

የያዘ መሆን አለበት።

## 10) <u>የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ስለመስጠት</u>

1stDRAFT

1. የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ሰጪው በዚህ መመሪያ አንቀጽ 8 መሠረት የተመለከቱትን መስፈርቶች መሟላታቸውን ካረጋገጠ በኋላ ተገቢውን የአገልግሎት ክፍያ በማስከፈል ለአመልካቹ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት መስጠት አለበት፡፡
2. አመልካቹ ያቀረበው ማመልከቻና ሰነዶች በዚህ መመሪያ መሠረት ተሟልቶ ያልቀረበ ወይም የተሳሳተ ወይም ሐሰተኛ በመሆኑ ተቀባይነት የሌለው መሆኑን የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ሰጪው ሲያረጋግጥ ያልተቀበለበትን ምክንያት ለአመልካቹ በጽሑፍ ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡

11) <u>የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለመውሰድ የሚፈጀው ጊዜ</u>

ማንኛውም ሰው የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለማግኘት ጥያቄውን በዚህ መመሪያ አንቀጽ 8 የተጠቀሱትን መስፈርቶች አሟልቶ ካቀረበበት ቀን ጀምሮ በሚቆጠር ቢበዛ በ30 ቀናት ውስጥ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀቱን ማግኘት ይኖርበታል፡፡

12) <u>የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የወሰደ ሰው መብት</u>

1. ያስመዘገበው የኢንዱስትሪ ኬሚካል ያመረተው ከሆነ ወደ ውጭ ሃገር የመላክ፣ በሀገር ውስጥ የመሸጥ፣ ማከፋፈል እና የማንቀሳቀስ መብት ይኖረዋል፣
2. ያስመዘገበው የኢንዱስትሪ ኬሚካል በአስመጭነት ለንግድ ዓላማ ከውጭ ሃገር ወደ ሃገር ውስጥ ያስገባው ከሆነ የመሸጥ፣ የማከፋፈልና የማሰራጨት መብት አለው፡፡
3. ያስመዘገበው የኢንዱስትሪ ኬሚካል በአስመጭነት ንግድ ነክ ላልሆነ ለግል አገልግሎት ወይም ለትምህርትና ሥልጠና ወይም ለምርምርና ስርጸት ወይም ለሌላ ተመሳሳይ ዓላማ ከውጭ ሀገር ወደ ሀገር ውስጥ ያስገባው ከሆነ ለዚሁ ዓላማ ብቻ የመጠቀም መብት ይኖረዋል፡፡

13) <u>የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የወሰደ ሰው ግዴታ</u>

1. የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀቱን ለሌላ ሦስተኛ ወገን እንዲጠቀምበት አሳልፎ ያለመስጠት፣
2. የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀቱን በግልፅ በሚታይ ቦታ ላይ የማስቀመጥ፣
3. የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀቱን በወቅቱ የማሳደስ፣

ISCDRAFT

4. የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀቱ ለሚሰጠው አገልግሎት የሚጠይቀውን ሙያዊ የሥነ-ምግባር ግዴታዎችን የማክበር፣
5. የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀቱን ሲወስድ ያሟላውን መስፈርት የማስቀጠል፣
6. በዚህ መመሪያ የተጠቀሱ ሌሎች ግዴታዎችን

የማክበር ግዴታ አለበት፡፡

14) <u>የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት መስፈርቶችን ስለመከለስ</u>

ሚኒስቴሩ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት መስፈርቶችን መጨመር ወይም መቀነስ አለበት ብሎ ካመነ በማንኛውም ጊዜ ሊከልስ ይችላል፡፡ ይህንንም ለሚመለከታቸው አካላት የተለያዩ የመረጃ ማሰራጫዎችን በመጠቀም እንዲያውቁት ሊያደርግ ይችላል፡፡

15) <u>ለውጥ ወይም ማስፋፊያ ስለማድረግ</u>

1. ማንኛውም የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የተሰጠው ሰው የአድራሻ ወይም የባለቤትነት ለውጥ ሲያደርግ ለብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ሰጪው በማሳወቅ አዲስ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ማግኘት አለበት ፡፡
2. ማንኛውም የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የተሰጠው ሰው የኬሚካል አገልግሎት ዘርፍ ለውጥ ለማድረግ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 8 የተገለጸውን መስፈርት ማሟላት ይጠበቅበታል፡፡
3. ማንኛውም የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የተሰጠው ሰው ተጨማሪ ማስፋፊያ ሲያደርግ አዲስ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ማግኘት አለበት፡፡
4. ማንኛውም የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ባለቤት የባለቤትነት ለውጥ ሲያደርግ በሕግ የተረጋገጠ ማስረጃ ማቅረብ አለበት፡፡

16) <u>ስለምትክ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት አሰጣጥ</u>

1. ማንኛውም የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የጠፋበት ወይም የተበላሸበት ወይም ሌላ ችግር ያጋጠመው ሰው ያቀረበው ምክንያት አጥጋቢ ከሆነ ወይም በቂ ማረጋገጫ ካቀረበ አስፈላጊውን የአገልግሎት ክፍያ በመክፈል ምትክ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት መውሰድ ይችላል፡፡

2. ምትክ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ሲሰጥ ቀድሞ የነበረው ኮድ ተሰርዞ አዲስ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ኮድ ይሰጠዋል፡፡

17) <u>የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ስለማሳደስ</u>

1. ማንኛውም የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ለሦስት ዓመታት ጸንቶ የሚቆይ ይሆናል፡፡
2. የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ጸንቶ የሚቆይበት ጊዜው ሲያበቃ ካልታደሰ አገልግሎት አይኖረውም፡፡
3. የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀትን ለማሳደስ መሟላት ያለባቸው መስፈርቶች፤
   ሀ/ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 8 የተዘረዘሩትን መረጃዎች አሟልቶ እና
   ለ/ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀቱ ባለቤት የምስክር ወረቀቱ ተፈጻሚነት የጊዜ ገደብ ከማለፉ ከአንድ ወር በፊት የእድሳት ማመልከቻውን ማቅረብ አለበት፡፡
4. የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀቱ የአገልግሎት ጊዜ ከተጠናቀቀ በኋላ በሁለት አመት ውስጥ ካልታደሰ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀቱ ይሰረዛል፡፡

<u>ክፍል ሦስት</u>

<u>ስለኢንዱስትሪ ኬሚካል ምዝገባ</u>

18) <u>የኢንዱስትሪ ኬሚካሎችን የማስመዝገብ ግዴታ</u>

1. ለማንኛውም ዓላማ የኢንዱስትሪ ኬሚካሎችን በሀገር ውስጥ የሚያመርት ሰው ስላመረተው ምርት ዝርዝር መረጃ በየወሩ ለሚኒስቴሩ የማስመዝገብ ግዴታ አለበት፡፡
2. ለማንኛውም ዓላማ የኢንዱስትሪ ኬሚካሎችን ወደ ሀገር ውስጥ የሚያስገባ ሰው ከማስገባቱ በፊት በየጊዜው ማስመዝገብ አለበት፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ 1 እና 2 የተመለከቱት ምዝገባዎች የሚከናወኑት ሚኒስቴሩ ለዚሁ አላማ ባዘጋጀው በይነ መረብ የምዝገባ አሰራር ስርዓት መሠረት ይሆናል፡፡

19) <u>የምዝገባ መስፈርት</u>

የኢንዱስትሪ ኬሚካሎችን ለማስመዝገብ የሚከተሉትን መስፈርቶችን መሟላት ይኖርባቸዋል፤

ሀ. ለዚሁ ዓላማ የተዘጋጀውን ቅጽ በመሙላትና በዚህ መመሪያ መሠረት የሚጠየቁትን ሰነዶች በማያያዝ ማቅረብ ፣

ለ. በዚህ መመሪያ መሠረት የተሰጠ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት፣

ሐ. አስመዝጋቢው አምራች ወይም አስመጪ ነጋዴ ከሆነ በንግድ ሥራ ላይ የሚገኝ መሆኑን የሚያሳይ የንግድ ሥራ ፈቃድ ወይም የኢንቨስትመንት ፈቃድ፣

መ. አስመዝጋቢው አስመጪ ሆኖ የኢንዱስትሪ ኬሚካሉን ወደ ሀገር ውስጥ ያስገባው ንግድ ነክ ላልሆነ ዓላማ ከሆነ እና ከሚመለከተው አካል የተሰጠ ወቅታዊ ደጋፊ ማስረጃ፣

ሠ. አስመዝጋቢው ወደ ንግድ ሥራ ለመግባት በሂደት ላይ ያለ አምራች ወይም አስመጪ ከሆነ እና ይህንኑ ሂደት መጀመሩን የሚያመለክት ከሚመለከተው አካል የተሰጠ ወቅታዊ ደጋፊ ማስረጃ፣

ረ. የኢንዱስትሪ ኬሚካሉ ትንተና የምስክር ወረቀት፤

I. የኢንዱስትሪ ኬሚካሉ አምራች ድርጅት ስም፣
II. የኢንዱስትሪ ኬሚካሉ ሳይንሳዊ መጠሪያ ስም፣
III. ድብልቅ የኢንዱስትሪ ኬሚካሉ አካላዊና ኬሚካላዊ ባህሪ የሚገልጽ ሰነድ፣
IV. የምርቱ መለያ ቁጥር፣
V. የኢንዱስትሪ ኬሚካሉ የተመረተበትና አገልግሎቱ የሚያበቃበት ጊዜ፣
VI. የኢንዱስትሪ ኬሚካሉ የሚሰጠው አገልግሎት፣

ሰ. ኮሜርሻል ወይም ፕሮፎርማ ኢንቮይስ፤

I. የኢንዱስትሪ ኬሚካሉ መጠሪያ ሥም፣
II. የኢንዱስትሪ ኬሚካሉ መጠን፣
III. የኢንዱስትሪ ኬሚካሉ የተመረተበት ሀገር፣
IV. የኢንዱስትሪ ኬሚካሉ የተጣጣመ የሸቀጦች አሰያየምና አመዳደብ ሥርዓት (Harmonized System Code(HS code))።

1st DRAFT

ሸ. የኢንዱስትሪ ኬሚካሉ የጭነት ዝርዝር መግለጫ (packing list) ወይም ለየብስ፣ለባህርና ለአየር ትራንስፖርት የጭነት ውል ክፍያ (Bill of Loading) ወይም ኤርዌይ ቢል (Airway Bill) የሚከተሉትን መረጃዎች የያዘ መሆን አለበት፤

I. የኬሚካሉ ዝርዝር፣ ዓይነትና መጠን፣ እና

II. የምርቱ መለያ ቁጥር፣

ቀ. የኢንዱስትሪ ኬሚካሉ ደህንነት መረጃ፣

I. የኢንዱስትሪ ኬሚካሉ መለያ ቁጥር (CAS number)፣

II. የኢንዱስትሪ ኬሚካሉ የጎጅነት ደረጃ (the hazardous category)፣

III. የኢንዱስትሪ ኬሚካሉ አያያዝና የጥንቃቄ ዘዴዎች፣

IV. የአደጋ ጊዜ መከላከያ መንገዶች።

በ. የስሪት ሀገር ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ፤

I. የላኪው ድርጅት ሥምና አድራሻ ፣

II. ኬሚካሉ የተመረተበት ሀገር፣

III. የማጓጓዣ ዘዴ፤

IV. የኢንዱስትሪ ኬሚክሉ ዓይነትና ዝርዝር ሁኔታ፤እና

V. የስሪት ሀገር ማረጋገጫ የምስክር ወረቀቱን የሰጠው የድርጅቱ ኃላፊ ስምና ፊርማ፤

ተ. በሦስተኛ ወገን የተረጋገጠ የጥራት ማረጋገጫ የምክስክር ወረቀት *(‹‹የጥራት ማረጋገጫ የምክስክር ወረቀት›› የሚለው ትርጉም ያስፈልገዋል። የእንግሊዘኛ ትርጉምም ያስፈልገዋል)*፣

ቸ. ከአምራች ወይም ከአቅራቢ ድርጅት ጋር የተገባ የውል ስምምነት፣

ኀ. በኢንዱስትሪ ኬሚካሉ እሽግ ላይ በግልፅ፣ በቀላሉ የሚነበብ እና የማይለቅ በእንግሊዘኛ ወይም በአማርኛ ቋንቋ የተፃፈ ገላጭ ጽሁፍ ሆኖ ቢያንስ፤

I. የኢንዱስትሪ ኬሚካሉ የምርት መለያ፤

ሀ) መጠሪያ ሥም፣

1st DRAFT

ለ) የሚሰጠው አገልግሎት አይነት፣

ሐ) ባች ቁጥር፡፡

II. የጽሁፍ መግለጫ (Signal word) *(ትርጉምም ያስፈልገዋል)*፣

ሀ) ማስጠንቀቂያ (Warning) *(ትርጉምም ያስፈልገዋል)*፣

ለ) አደጋ (Danger) *(ትርጉምም ያስፈልገዋል)*፣

III. የአደጋ መግለጫ (Hazard statements) *(ትርጉምም ያስፈልገዋል)*፣

IV. የጥንቃቄ መግለጫ (Precautionary Statements) *(ትርጉምም ያስፈልገዋል)*
፣

V. የንጥረ ነገር ይዘት(chemical Composition) *(ትርጉምም ያስፈልገዋል)*፣

VI. የስዕል መግለጫዎች (Pictograms) *(ትርጉምም ያስፈልገዋል)*፣

VII. የኢንዱስትሪ ኬሚካሉ የተመረተበት ሀገር፣

VIII. የአምራቹ ድርጅት ሥም እና አድራሻ፣

IX. የኢንዱስትሪ ኬሚካሉ የተመረተበት እና አገልግሎቱ የሚያበቃበት ጊዜ
የሚገልጽ መሆን አለበት፡፡

ነ. በአዋጁ አንቀጽ 5 መሠረት ጥብቅ የአጠቃቀም ገደብ የተጣለባቸው የኢንዱስትሪ ኬሚካሎች አምራች ወይም አስመጪ ከአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን የተሰጠ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት፣

ኘ. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (ነ) የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ የኬሚካሉ የአገልግሎት ጊዜ ከ18 ወራት በታች ከሆነ ከአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን የተሰጠ የልዩ ፈቃድ ሊኖረው ይገባል፡፡

20) <u>የማስረጃዎች ትክክለኛነት ስለማረጋገጥ</u>፣

የምስክር ወረቀት ሰጪው የኢንዱስትሪ ኬሚካሎችን ሲመዘግብ በየጊዜው በአስመዝጋቢዎች የሚቀርቡ ሰነዶችን ትክክለኛነት ማረጋገጥ አለበት፡፡

21) <u>የኢንዱስትሪ ኬሚካሎች የምዝገባ ሂደት የሚወስደው ጊዜ</u>

የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ሰጪው የምዝገባ ማመልከቻ ከቀረበበት ቀን ጀምሮ አስፈላጊ መረጃዎችን አሟልቶ ሲገኝ ከሶስት እስከ ሰባት ባሉት ቀናት ውስጥ የምዝገባ ሂደቱ መጠናቀቅ አለበት፡፡

1st DRAFT

22) <u>የኢንዱስትሪ ኬሚካሎች መዝገብ ይዘት</u>

የኢንዱስትሪ ኬሚካሎች ምዝገባ የሚሰፍርበት ባሕር መዝገብ ወይም በይነ መዝገብ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 19 (የምዝገባ መስፈርት) ላይ የተጠቀሱትን የምዝገባ መስፈርቶችን አካቶ መያዝ ይኖርበታል፡፡

23) <u>የምዝገባ ማረጋገጫ ስለመስጠት</u>

የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ሰጪው፤ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 19(የምዝገባ መስፈርት) ላይ የተጠቀሱትን የምዝገባ መስፈርት አሟልቶ ለተመዘገበ የኢንዱስትሪ ኬሚካል ለአስመዝጋቢው የምዝገባ ማረጋገጫ ደብዳቤ መስጠት አለበት፡፡

24) <u>የኢንዱስትሪ ኬሚካል ያስመዘገበ ሰው ግዴታ</u>

1. ያስመዘገበውን ኬሚካል መረጃ በአግባቡ የመያዝ፣
2. ያመረተው ወይም ያስገባው ኬሚካል የአገልግሎት ጊዜው ከማለፉ ሦስት ወራት በፊት ተጠቅሞ መጨረስ ወይም ለሌሎች ተጠቃሚዎች የማስተላለፍ፣
3. በበጀት ዓመቱ መጨረሻ የተጠቀመውን፣ ለሌሎች ያስተላለፈውን፣ በአያየዝ ጉድለት የተበላሸ ወይም የመጠቀሚያ ጊዜው ያለፈበትን ኬሚካል ዓይነትና መጠን መረጃ አደራጅቶ በመያዝ ለሚኒስቴሩ ሪፖርት የማድረግ፣
4. በአያያዝና በአጠቃቀም ሂደት ያጋጠመ ጉዳት ካለ የማሳወቅ፣
5. በደህንነትና በቴክኒካል ዳታ ሺት(MSDS/MTDS)መሠረት ኬሚካሎችን የመያዝና የመጠቀም፣
6. ካስመዘገበው የኢንዱስትሪ ኬሚካል ጋር ግንኙነትና ቀረቤታ ላላቸው ሰዎች ስለኬሚካሉ አጠቃቀምና ስለሚያደርሱት ጉዳት እንዲሁም ስለደህንነት ማስጠበቂያ መሳሪያዎች ጥቅም ግንዛቤ የመፍጠር፣
7. ካስመዘገበው የኢንዱስትሪ ኬሚካል ጋር ግንኙነትና ቀረቤታ ላላቸው ሰዎች የደህንነት መጠበቂያ መሳሪያዎችን የሚሟላትና እንዲጠቀሙ የማድረግ፡፡

25) <u>እንደገና ስለማስመዝገብ</u>

1st DRAFT

አንድ የተመዘገበ ኢንዱስትሪ ኬሚካል በማንኛውም ሁኔታ ቀድሞ ከነበረው ንጥረ ነገር ይዘት ወይም ባህሪ ከተቀየረ ወይም ስለኬሚካሉ ጎጂነት በምዝገባ ወቅት ያልታየ አዲስ መረጃ ከተገኘ ወይም አጠቃቀሙ ከተለወጠ እንደገና መመዝገብ አለበት፡፡

26) <u>ምዝገባን ስለመሰረዝ</u>

ከሚከተሉት ምክንያቶች በአንዱ ምዝገባ ይሰረዛል፤

ሀ) የተመዘገበው የኢንዱስትሪ ኬሚካል ጥቅም ላይ እንዳይውል የተከለከለ ከሆነ፤

ለ) የተመዘገበው የኢንዱስትሪ ኬሚካል በሰው ወይም በእንስሳት ጤና ወይም በአካባቢ ላይ ጉዳት የሚያደርስ መሆኑን የሚያረጋግጥ አዲስ መረጃ ሲገኝ እና ጉዳቱን ለማስቀረት ወይም ወደ ኢምንት ደረጃ ለማድረስ የማይቻል መሆኑ ሲታወቅ፤

ሐ) በምዝገባ ወቅት የቀረቡ ማስረጃዎች ትክክል ያልሆኑና የተሳሳተ መሆኑ ሲረጋገጥ፤

መ) ምዝገባው የተፈቀደው በአዋጁ ወይም በዚህ መመሪያ የተቀመጡ መስፈርቶችን የጣሰ መሆኑን ሲረጋገጥ፡፡

## <u>ክፍል አራት</u>

## <u>የኢንዱስትሪ ኬሚካል ክትትል እና አስተዳደራዊ እርምጃዎች</u>

27) <u>ሪፖርት ስለማቅረብ</u>፣

1. ማንኛውም የኢንዱስትሪ ኬሚካል አምራች ወይም አስመጪ በአንቀጽ 28(ስለማስረጃ አያያዝ) የተጠቀሱትን መረጃዎችን በየዓመቱ ከሐምሌ 1 እስክ 30 ባለው ጊዜ ውስጥ ለሚኒስቴሩ በጽሑፍ ሪፖረት ማቅረብ አለበት፣

2. ማንኛውም የኢንዱስትሪ ኬሚካል አምራች ወይም አስመጪ በይዞታው ስር የሚገኙ የኢንዱስትሪ ኬሚካሎች በስርቆት ወይም በኃይል ወይም በሌላ መሰል ሁኔታዎች ወደ ሶስተኛ ወገን የተላላፈ ከሆነ በ 48 ሰዓታት ውስጥ አግባብነት ላለው አካል ሪፖርት ማድረግ አለበት፡፡

28) <u>ስለማስረጃ አያያዝ</u>፣

1st DRAFT

1. ማንኛውም የኢንዱስትሪ ኬሚካል አምራች ወይም አስመጪ በአንቀጽ 27 (ሪፖርት ስለማቅረብ) መሠረት ለሚኒስቴሩ የሚያቀርበው ሪፖርት የሚከተሉትን መረጃዎች መያዝ አለበት፤

ሀ. ያመረተውን፣ ወደ ውጭ ሀገር የላከውን፣ ያከፋፈለውን፣ ወደ ሀገር ውስጥ ያስገባውን፣ የተጠቀመውን እና በሌላ በማንኛውም ምክንያት እጁ ላይ የሚገኘውን የኢንዱስትሪ ኬሚካል ዓይነትና መጠን፣

ለ. በሀገር ውስጥ ገበያ የሸጠውን እና ያከፋፈለውን ኬሚካል ዓይነትና መጠን፣

ሐ.በአያያዝ ጉድለትና የተበላሹ ወይም የመጠቀሚያ ጊዜ ያለፈባቸውን የኢንዱስትሪ ኬሚካሎች ዓይነትና መጠን፣

መ.የኢንዱስሪ ኬሚካሎች የተመረቱበት ሀገር ፣ያመረተው ድርጅት ስምና አድራሻ፣

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ (1) ላይ የተመለከቱት መረጃዎች ቢያንስ ለ5 ዓመት ተይዘው መቆየት አለባቸው፣

3. ማንኛውም የኢንዱስትሪ ኬሚካል አምራች ወይም አስመጪ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ (1) የተጠቀሱት ማስረጃዎችን በኮሞፒውተረ በመጠቀም ለትንተና እና ለበለጠ ማብራሪያ በሚጠቅም መልኩ በዲጅታል ኢንኮድንግ ሲስተም መረጃ መያዝ አለበት፡፡

29) <u>ስለናሙና አወሳሰድ፤</u>

አጠራጣሪ ሁኔታ ሲገጥም ሚኒስቴሩ ለምርመራ የሚሆን ናሙና ከማንኛውም የኢንዱስትሪ ኬሚካሎችን አምራች ወይም ከውጭ ሀገር ወደ ሀገር ውስጥ የሚያስገባ አስመጪ ያለክፍያ በነፃ ሊወስድ ይችላል፡፡

30) <u>የኢንዱስትሪ ኬሚካሎች ቁጥጥር</u>

1. የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ሰጪው ማንኛውም ሰው ያስመዘገበውን የኢንዱስትሪ ኬሚካል አያያዝና አጠቃቀም በዓመት ሁለት ጊዜ ወይም አስፈላጊ ሆኖ ባገኘው ጊዜ የመስክ ኢንስፔክሽን ወይም ምልከታ በማድረግ ሊገመግም ይችላል፣

1stDRAFT

2. በብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ሰጪው የኢንስፔክሽን ወይም የምልከታ ሪፖርት መሠረት የተገኘ ጉድለት ካለ ለማስተካከል የእርምት እርምጃ በሚኒስቴሩ በኩል እንዲወሰድ ይደረጋል፡፡

3. ማንኛውም ሰው ያስመዘገበውን የኢንዱስትሪ ኬሚካሎች አያያዝና አጠቃቀም በተመለከተ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ሰጪው ባለሙያ በኢንዱስትሪ ኬሚካል አምራቹ ወይም በአስመጪው ድርጅት ገብተው የኢንስፔክሽን ወይም የምልከታ ሥራ እንዲሰሩ አስፈላጊውን ትብብር እና መረጃዎችን የመስጠት ግዴታ አለበት፡፡

31) <u>የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ሰጪው ባለሙያ ግዴታ</u>

የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ሰጪው ባለሙያ ማንኛውም የኢንዱስትሪ ኬሚካል አምራች ወይም አስመጪን በመጥራት ወይም ከድርጅቱ በመግባት የኢንስፔክሽን ወይም የምልከታ ሥራ ለመሥራት፤

ሀ) የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ሰጪው የሥራ ክፍል ሠራተኛ መሆኑን የሚያረጋግጥ በሚኒስቴሩ የተሰጠ የሠራተኛነት መታወቂያ ወረቀት መያዝ፣

ለ) የኢንስፔክሽን ወይም ምልከታ ሥራ እንዲሰራ የሚያመለክት በብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ሰጪው ኃላፊ የተፈረመ ደብዳቤ መያዝ፣

ሐ) ናሙና ሲወስድ ደረሰኝ ወይም የመረከቢያ ሰነድ የመስጠት፤

መ) በሥራ አጋጣሚ ያገኘውን ማንኛውንም መረጃ ወይም ሰነድ በሚስጥር የመያዝ ይኖርበታል፡፡

32) <u>የኢንስፔክሽን ወይም የምልከታ ሥራ ሪፖርት አቀራረብ</u>

የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ሰጪው ባለሙያ በአንቀጽ 30 የኢንዱስትሪ ኬሚካሎች ቁጥጥር መሠረት ኢንስፔክሽን ወይም ምልከታ ካደረገ በኋላ በሦስት ቀን ውስጥ ሪፖርቱን ለብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ሰጪው ኃላፊ በጽሑፍ ማቅረብ አለበት፡፡

33) <u>የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ወይም የምዝገባ ማረጋገጫ ስለሚታገድበት ሁኔታ</u>

1st DRAFT

ጉዳዩ ይመለከተኛል በሚል ማንኛውም ሦስተኛ ወገን አመልካችነት ወይም በሚኒስቴሩ አነሳሽነት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ወይም የምዝገባ ማረጋገጫ ደብዳቤ ያለአግባብ ስለመሰጠቱ ሲደረስበትና የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀቱ ወይም የምዝገባ ማረጋገጫ ካልታገደ በቀር ጉዳት የሚያደርስ መሆኑን ሲረጋገጥ ሚኒስቴሩ በጊዜያዊነት ሊያግደው ይችላል፡፡

34) <u>የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ወይም የምዝገባ ማረጋገጫ ስለሚሰረዝበትና በድጋሚ ስለሚወሰድበት ሁኔታ</u>

1. በአዋጁ አንቀጽ 15 የተጠቀሱት የወንጀል ቅጣቶች እንደተጠበቁ ሆነው ማንኛውም ሰው ከዚህ በታች በተመለከቱት ምክንያቶች በአንዱ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ወይም የምዝገባ ማረጋገጫ ሊሰርዝበት ይችላል፤

ሀ) የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀቱ ወይም የምዝገባ ማረጋገጫው የወሰደበትን ሥራ በማናቸውም ምክንያት የተወ እንደሆነ፣

ለ) የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀቱ እንዲሰረዝለት ሲጠይቅ፣

ሐ) የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ወይም የምዝገባ ማረጋገጫ የወሰደበትን ሥራ መሥራት እንደማይችል አስተዳደራዊ እርምጃ ሲወሰድበት ወይም በፍርድ ቤት ሲወሰንበት፣

መ) የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ወይም የምዝገባ ማረጋገጫው የወሰደው ሀሰተኛ መረጃ ወይም ሰነድ አቅርቦ ከሆነ፣

ሠ) ሙያው የሚጠይቀውን የሙያ ሥነ-ምግባር የጣሰ እንደሆነ፣

ረ) የወሰደው የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ሳያሳድስ ከሁለት ዓመት በላይ የቆየ ከሆነ፣

ሰ) ሥራውን የማከናወን ችሎታ ያጣ ከሆነ፣

ሸ) የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ሰጪ ኃላፊን ወይም ባለሙያን ያሳሳተ ወይም ያታለለ እንደሆነ፣

ቀ) ለምርመራ የሰጠው ናሙና በትክክል የኢንዱስትሪ ኬሚካሉን እንዳይወክል ያዛባ እንደሆነ፤

በ) በዚህ መመሪያ ከተደነገገው ውጪ የኢንዱስትሪ ኬሚካልን ያከማቸ፣የተጠቀመ፣ ያጓጓዘ እንደሆነ፤

ተ) ሆን ብሎ ኬሚካል መያዣ ላይ ማንኛውንም መለያ የገነጠለ፣የለወጠ፣ያበላሸ ወይም ያጠፋ እንደሆነ፤

ቸ) ሆን ብሎ የኢንዱስትሪ ኬሚካል የተመለከተን መረጃ የደበቀ እንደሆነ፤

ኀ) የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ሰጪ ኃላፊ ወይም ባለሙያ በዚህ መመሪያ መሠረት ተግባሩን ለመወጣት መረጃ ሲጠይቅ ለመተባበር ፈቃደኛ ያልሆነ እንደሆነ፤

ነ) ሆን ብሎ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ሰጪ ኃላፊን ወይም ባለሙያ የታሸገውን መጋዘን የከፈተ እንደሆነ፤

ኘ) በአዋጁ ወይም በመመሪያው የተደነገጉትን መስፈርቶች ያላሟላ ከሆነ፣

አ) የአዋጁን ወይም የመመሪያውን አስገዳጅ ድንጋጌዎች የጣሰ ከሆነ፣

ከ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ ከዚህ በላይ ከተጠቀሱት ውጪ በማንኛውም መንገድ የአዋጁን ወይም የመመሪያውን አፈጻጸም የሚያሰናክል ወይም የሚጎዳ ተግባር በማድረግ ወይም ባለማድረግ የፈጸመ ከሆነ።

2. የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ሰጪው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀቱን ወይም የምዝገባ ማረጋገጫ ከመሰረዙ በፊት ባለጉዳዩ የመቃወሚያ ሐሳብ ካለው እንዲያቀርብ ባስመዘገበው አድራሻው በደብዳቤ ማሳወቅ አለበት፣
3. ባለጉዳዩ ደብዳቤው በደረሰው በ10 የሥራ ቀናት ውስጥ የመቃወሚያ ሀሳብ ካላቀረበ ወይም ያቀረበው የመቃወሚያ ሀሳብ የሕግ መሠረት የሌለው ከሆነ ወይም ባስመዘገበው አድራሻ ሊገኝ ካልቻለ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀቱ ወይም የምዝገባ ማረጋገጫው ይሰረዛል፣

1st DRAFT

4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1(ሐ)፣(መ) ፣(ሠ) እና (ረ) መሠረት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ወይም የምዝገባ ማረጋገጫ የተሰረዘበት ሰው እንደገና የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ወይም የምዝገባ ማረጋገጫ እንዲሰጠው በዚህ መመሪያ አንቀጽ 8 የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት መስፈርት እና አንቀጽ 19 የምዝገባ መስፈርት ከተገለጹት መስፈርቶች በተጨማሪ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ወይም የምዝገባ ማረጋገጫ እንዳይሰጠው የሚከለክል አስተዳደራዊ ቅጣት ወይም የፍርድ ቤት ውሳኔ የሌለ መሆኑን ማረጋገጫ ከሚመለከተው አካል ማቅረብ ይኖርበታል፣
5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት የተሰረዘን የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት እንደገና መውሰድ የሚቻለው ከተሰረዘበት ቀን ጀምሮ በሚታሰብ ከአንድ ዓመት በኋላ ይሆናል፡፡

35) ***መረጃዎች ተደራሽ ስለማድረግ***

ሚኒስቴሩ የሚከተሉትን መረጃዎች ለኅብረተሰቡ ተደራሽ ማድረግ አለበት፤

ሀ) በዚህ መመሪያ መሠረት የተሰጡ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ዝርዝር፣
ለ) በየጊዜው የተመዘገቡ የኢንዱስትሪ ኬሚካሎች ዝርዝር፤
ሐ) በየጊዜው ከምዝገባ የተሰረዙ የኢንዱስትሪ ኬሚካሎችን ዝርዝር እና
መ) በዚህ መመሪያ አንቀጽ 38 ==(መዝገብ ስለማደራጀት)== እና አንቀጽ 39 ==(ብሔራዊ የኬሚካል መዝገብ==) መሠረት የተደራጁ መረጃዎች፡፡

36) ***መረጃዎችን ይፋ ስለማድረግ***

1. ማንኛውም የኢንዱስትሪ ኬሚካል አምራች ወይም አስመጪ ወይም ሌላ ማንኛውም ሰው ከኢንዱስትሪ ኬሚካል እንቅስቃሴ ጋር በተያያዘ ከአዋጁ እና ከዚህ መመሪያ ውጪ ከፈጸመ እና ለሕዝብ ጥቅም አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ፣

2. ሚኒስቴሩ ማንኛውም የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ወይም የምዝገባ ማረጋገጫ ደብዳቤ የታገደበትን፣ ያልታደሰበትን ወይም የተሰረዘበትን ምክንያት ለሕዝብ ጥቅም አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ፣

ሚኒስቴሩ መረጃዎችን በማንኛውም የመገናኛ ዘዴ ይፋ ሊያደርግ ይችላል፡፡

## <u>ክፍል አምስት</u>

## ብሔራዊ የኬሚካል መዝገብ ስለማደራጀትና የመዝገቡን ይዘት ስለመወሰን

37) **መዝገብ ስለማደራጀት**

ሚኒስቴሩ በሀገሪቱ ያሉ የኢንዱስትሪ ኬሚካሎችን እና አግባብ ያላቸው አካላት የሚያስተዳድሯቸው ኬሚካሎችን መረጃ ለመያዝ የሚያስችለው ብሔራዊ የኬሚካል መዝገብ ያደራጃል፡፡

38) **የብሔራዊ የኬሚካል መዝገብ ይዘት**

የሚደራጀው ብሔራዊ የኬሚካል መዝገብ ቢያንስ፤

ሀ) የኬሚካል ምዝገባ ቁጥር፣

ለ) የኬሚካሉ ሳይንሳዊ መጠሪያ ስም፣

ሐ) የኬሚካሉ የምርት ወይም የንግድ ስም፣

መ) ኤች ኤስ ኮድ፣

ሠ) የኬሚካል መለያ ቁጥር፣

ረ) የጎጂነት ባህሪ ምደባ፣

ሰ) የአገልግሎት አይነት፣

ሸ) የተመረተበት እና አገልግሎቱ የሚያበቃበት ቀን፣

ቀ) የአምራቹ ወይም የአስመጪው ስምና አድራሻ፣

በ) የኬሚካሉ መጠን፣

መረጃዎችን መያዝ አለበት፡፡

39) **አግባብ ያላቸው አካላት የሚያስተዳድሯቸው ኬሚካሎች መረጃ ስለመላክ**

አግባብ ያላቸው አካላት ስለሚያስተዳድሯቸው ኬሚካሎች የተመለከቱ መረጃዎችን በየዓመቱ ከሐምሌ 1 እስከ 30 ባሉት ቀናት ውስጥ ለሚኒስቴሩ መላክ አለባቸው፡፡

40) **በብሔራዊ የኬሚካል መዝገብ የተደራጁትን መረጃዎች ስለመላክ**

ሚኒስቴሩ፤ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 38 እና 39 መሠረት አደራጅቶ የያዛቸውን የኢንዱስትሪ ኬሚካል እና አግባብነት ያላቸው አካላት የሚያስተዳድሯቸው ኬሚካሎች

1st DRAFT

መረጃዎችን ከነሐሴ 1 እስከ 30 ባሉት ቀናት ውስጥ ለአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን መላክ አለበት፡፡

## ክፍል ስድስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

41) **ቅሬታ ስለማቅረብ**

1. በዚህ መመሪያ በሚሸፈን በማናቸውም ጉዳይ ቅሬታ ያለው ባለጉዳይ ወይም ጉዳዩ የሚመለከተው ሦስተኛ ወገን ቅሬታ የሚያቀርብበት ጉዳይ ውሳኔ ባገኘ በ10 የሥራ ቀናት ውስጥ ለብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ሰጪው የቅሬታ አቤቱታ ማቅረብ ይችላል፤
2. የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ሰጪው የቀረበውን አቤቱታ ሰምቶ በ10 የሥራ ቀናት ውስጥ ውሳኔውን ለባለጉዳዩ በጽሁፍ ማሳወቅ አለበት፡፡ ሆኖም በተጠቀሱት ቀናት ውስጥ ውሳኔውን ያላሳወቀው እንደሆነ ቅሬታ አቅራቢው ለሚኒስቴሩ አቤቱታውን ማቅረብ ይችላል፡፡ ሚኒስቴሩ በ15 የሥራ ቀናት ውስጥ ውሳኔ ካልሰጠው ቅሬታ አቅራቢው ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት አቤቱታውን ማቅረብ ይችላል፤
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት ሚኒስቴሩ በሰጠው ውሳኔ ላይ በሕግ ጉዳይ ረገድ ቅሬታ ያለው ማንኛውም ሰው ቅሬታ የቀረበበት ጉዳይ ውሳኔ በተሰጠ በ60 ቀናት ውስጥ ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት ይግባኝ ማቅረብ ይችላል፡፡

42) **ስለ አገልግሎት ክፍያ**

በዚህ መመሪያ መሠረት ሚኒስቴሩ ለሚሰጠው አገልግሎት የሚያስከፍለው የአገልግሎት ክፍያ ከዚህ መመሪያ ጋር በተያያዘው የገንዘብ ሚኒስቴር ውሳኔ መሠረት የሚፈጸም ይሆናል፡፡

43) **የመተባበር ግዴታ**

ማንኛውም የኢንዱስትሪ ኬሚካል አምራች ወይም አስመጪ ለዚህ መመሪያ አፈጻጸም ለምስክር ወረቀት ሰጪው ኃላፊ ወይም ለባለሙያ ወይም ሚኒስቴሩ ለሚወክለው ሌላ ሰው አስፈላጊውን ትብብር የማድረግ ግዴታ አለበት፡፡

44) **የሽግግር ሁኔታ**

1. ይህ መመሪያ ከመጽደቁ በፊት በሥራ ላይ የሚገኝ ማንኛውም የኢንዱስትሪ ኬሚካል አምራች ወይም አስመጪ ይህ መመሪያ ከጸደቀበት ቀን ጀምሮ በስድስት ወር የጊዜ ገደብ ውስጥ በዚህ በመመሪያ መሠረት ከሚኒስቴሩ የተሰጠ የምስክር ወረቀት ወይም የምዝገባ ማረጋገጫ ሊኖረው ይገባል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተጠቀሰው የጊዜ ገደብ ካለፈ በኋላ ከሚኒስቴሩ የተሰጠ የምስክር ወረቀት ወይም የምዝገባ ማረጋገጫ ሳይኖረው በኢንዱስትሪ ኬሚካል እንቅስቃሴ በተሳተፈ በማንኛውም ሰው ላይ ሚኒስቴሩ፤
   ሀ) በአዋጁ አንቀጽ 15 እና አግባብነት ባለው በሌሎች ሕጎች መሠረት በወንጀል ተጠያቂ እንዲሆን፣
   ለ) ከሚመለከተው መንግሥታዊ አካል ጋር ግንኙነት በማድረግ የንግድ ፈቃዱ እንዲሰረዝ ፣ እና
   ሐ) ከሚመለከተው መንግሥታዊ አካል ጋር ግንኙነት በማድረግ በእጁ የሚገኑ የኢንዱስትሪ ኬሚካሎች በመንግሥት እንዲወረሱ

አስፈላጊውን ያደርጋል፡፡

## 45) <u>*መመሪያውን ስለማሻሻል*</u>

ይህ መመሪያ እንደአስፈላጊነቱ በማንኛውም ጊዜ በሚኒስቴሩ ሊሻሻል ይችላል፡፡

## 46) <u>*የተሻሩና ተፈጻሚነት የሌላቸው አሠራሮችና መመሪያዎች*</u>

1. የኢንዱስትሪ ኬሚካል ከብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀትአሰጣጥ፣ ከምዝገባና ከመረጃ አያያዝ ጋር የተያያዙ አሠራሮችና መመሪያዎች በዚህ መመሪያ ተሽረዋል፡፡
2. አግባብ ያላቸው አካላት የሚያስተዳድሯቸው ኬሚካሎች በአዋጁ እና በዚህ መመሪያ ከተጠቀሱ መረጃ አያያዝ ጋር የተያያዙ አሠራሮችና መመሪያዎች በዚህ መመሪያ ተሽረዋል፡፡
3. ይህንን መመሪያ የሚቃረን ማንኛውም መመሪያ ወይም ሰርኩላር ደብዳቤ ወይም አሠራር በዚህ መመሪያ ውስጥ ለተመለከቱ ጉዳዮችን ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

## 47) <u>*መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ*</u>

1st DRAFT

ይህ መመሪያ በሚኒስትሩ ጸድቆ፣በፍትሕ ሚኒስቴር ተመዝግቦ እና በሚኒስቴሩ ድረ-ገጽ ላይ ከተጫነበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ፣ ኅዳር- - - ቀን 2017ዓ.ም

መላኩ አለበል አዲስ
የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ሚኒስትር

1st DRAFT

## <u>ቅፅ /Annex/ I</u>

**የኢንዱስትሪ ኬሚካል አስመጪ ማመልቻ ቅፅ /application form for industrial chemical importer/**

**1. የአመልካች ሙሉ አድራሻ /Full Address of Applicant /**

የአስመጪው ድርጅት ሙሉ ስም /Importer Company Full name/……………………………………………………………….

አድራሻ/Address/ ………………………………. ክ/ከተማ/sub city/……………………..ወረዳ/woreda/………………

ስ.ቁጥር /Phone no/…………………………………………………ኢ.ሜል/ Email/……………………………………………………

የንግድ ፈቃድ ቁጥር /Trade License Number/…………………………………………………………………………………….

ቲን ቁጥር /Tin No/………………………………………………………………………………………………………………………

የንግድ ፈቃድ አይነት /Trade license category/ ………………………………………………………………………………..

የድርጅቱ ዋና ስራ አስኪያጅ ሙሉ ስም/company general full name/…………………………………………………….......

አድራሻ/Address/…………………………………ክ/ከተማ/subcity/……………………..ወረዳ/woreda/……………………..

ስ.ቁጥር /Phone no/…………………………………………………ኢ.ሜል/ Email/………………………………………………

## 2. ወደ ሀገር ውስጥ የሚገባው ኬሚካል መረጃ /Imported Chemical Information/

የኬሚካሉ ስም /Chemical trade Name/……………………………………………………………………………………………

ሳይንሳዊ የኬሚካሉ መጠሪያ ስም /scientific chemical name /…………………………………………………………

የተመረተበት ሀገር /country of origin/…………………………………………………………………………………………..

የተመረተበት ቀን /Manufacturing date/……………….የአገልግሎት ማብቂያ ቀን /Expired date/……………………….

ኬሚካሉን የመረተው ድርጅት ሙሉ ስም /Chemical Manufacture Full Name/……………………………………..

## ቅፅ /Annex/ 2
## የኢንዱስትሪ ኬሚካል ለማስመዝገብ የሚያስፈልጉ መስፈርቶች (requirements to register industrial chemical)

1. የኢንዱስትሪ ኬሚካል አስመጪነት የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት/Industrial chemical import competency certificate/

2. የኢንዱስትሪ ኬሚካል አስመጪነት ንግድ ፈቃድ/Industrial chemical import business license/
3. የአምራችነት/ኢንቨስትመት/ ፈቃድ /Manufacturing /investment/license/
4. የንግድ ክፍያ መጠየቂያ /commercial invoices/
5. የጭነቱ ዝርዝር /Packing list/
6. የመጫኛ ሂሳብ /bill of loading /
7. የስሪት ሀገር ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት /certificate of origin/
8. የኬሚካላዊ ትንተና የምስክር ወረቀት/chemical certificate of analysis/
9. የኬሚካሉ ደህንነት መረጃ ወረቀት/chemical Material Safety data sheet /
10. ኬሚካሉ ከሌላ ተቋም የቅድመ ማስገቢያ ፈቃድ የሚያስፈልገው ከሆነ ከሚመለከተው ተቋም የተሰጠ የማስገቢያ ፈቃድ ደብዳቤ/የምስክር ወረቀት /if the chemical requires a pre-entry permit from another institution, Entry permission letter from the concerned institution required/

1st DRAFT

## ቅፅ /Annex/ 3

በመመሪያው የሚሸፈኑ የኢንዱስትሪ ኬሚካሎችን የአስመጪነት የምስክር ወረቀት ለማግኘት መሟላት ያለባቸው መስፈርቶች/Requirements to be met to obtain a certificate for industrial chemical importation/

| S.no | መስፈርቶች /Requirements/ | አስተያየት/remarks/ |
|---|---|---|
| 1. | ማመልከቻ ቅፅ/ Application form/ | |
| 2. | የኢንዱስትሪ ኬሚካል አስመጪነት ንግድ ፈቃድ/Industrial chemical import business license/ | |
| 3. | የአምራችንት/ኢንቨስትመት/ ፈቃድ /Manufacturing /investment/license/ | |
| 4. | ደረጃውን የጠበቀ የኬሚካል ማስቀመጫ መጋዘን የይዞታ ማረጋገጫ ሰነድ /ህጋዊ የክራይ ውል/Certificate of ownership of standard chemical storage warehouse /Legal Lease Agreement// | |
| 5. | የመጋዘን ጂ.ፒኤስ ኤክስ ዋይ ኮርድኔሽን/Warehouse GPS X Y Coordination/ | |
| 6. | በዘርፍ (በኬሚካል አያያዝ ስርዓት)የሰለጠነ ተገቢ የሆነ ባለሙያ መቅጠሩን የሚያረጋግጥ ሰነድ (A document confirming the employment of an appropriate professional trained in the field (chemical management system)). | |
| 7. | ደረጃውን የጠበቀ የአስተዳደር ቢሮ/standard administration offices with full office equipment's/ | |
| 8. | ደረጃውን የጠበቀ የእሳት አደጋ መከላከያና መቆጣጠሪያ ስርዓት /Standard Fire Protection and Control System/ | |
| 9. | የድንገተኛ አደጋ መከላከያ እና መቆጣጠሪያ ስርዓት /standard Emergency prevention and control system/ | |
| 10. | | |

1st DRAFT